# Thirdmill Institute
## Trainer Orientation

## የአሰልጣኝ መመሪያ

*ተርድሚል ኢንስቲቱት ነፃ እዉቅና ያለዉ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ስልጠና በመስጠት ቤተክርስትያንን እና በየሀገሩ ያሉ መሪዎችን እያስተማረ ያስታጥቃል፡፡*

### ተርድሚል ኢንስቲቱት ማን ነዉ?

ሪቻርድ ፕራት እና ተርድሚል ሚኒስትሪ ከ20 ዓመት በላይ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ለአለም ሁሉ በነፃ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ትምህርቶቹ በማህደረ ብዙ በሆነ መልክ በጥሩ ጥራት ይሰጣል፡፡ ብዙ የመፅሀፍ ቅዱስ ት/ቤቶች እና ሴሚናሪዎች የሚያስተምሩትን ያስተምራል፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ወደ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው የእግዝአብሔርን ቃል የበለጠ ለመማር ለሚሹ ሁሉ በነፃ ይሰጣሉ፡፡ ትምህርቶቹ ቅድመ ተከተል የሌላቸዉ ስለሆነ ስርአተ ትምህርቱ ለብዙ ባህሎች እና አዉዶች መሆን እንዲችል አድርጎታል፡፡

ተርድሚል ኢንስቲቱት አዲስ ነገር ይዞ ነዉ የመጣዉ፡፡ ትምህርቶችን በማዋቀር ወደ የተለያዩ ኮርሶች በመለወጥ ለተማሪዎች እና አሰልጣኞች ጥራት ያለዉ ትምህርት እና በማህበረሰባቸዉ ዉስጥ ጥሩ የመማሪያ ጊዜ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፡፡ ተርድሚል ኢንስቲቱት መደበኛ አካሄድ እንደሚያስፈልገዉ በማወቅ ስርአት ትምህርቱን ወደ ሶስት የሰርተፊኬት ፕሮግራሞች ከፋፍሏል፡፡ የሰርተፊኬት ፕሮግራሞቹ ሁሉ በየጊዜው የሚሰሩ ስራዎች አሏቸው፡፡ ተማሪዉ ሶስቱንም ሰርተፊኬት ካገኘ በዉሀላ ዲፕሎማ ይሰጠዋል፡፡ ለዚህ ሁሉ መሳካት ደሞ አሰልጣኝ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የዚህ ኢንስቲቱት አላማ ሶስት ነዉ፡፡ አንደኛ ተማሪው የተማረዉን ተረድቶ ወደ ዉስጡ እንዲያስገባዉ፡፡ ሁለተኛ ተማሪው የተማረዉን ወደ ሚኒስትሪዉ አምጥቶ ጥቅም ላይ ማዋል፡፡ ሶስተኛ ተማሪዎች የተማሩት ትምህርት ከእግዝአብሔር ጋር ያላቸዉን ግንኙነት እንዲያጠነክር እና በቃሉ ማደግ እንዲችሉ ነዉ፡፡

### የአሰልጣኝ ድርሻ ምንድ ነዉ?

አሰልጣኝ እንደመሆንህ ለተማሪዎችህ ስኬት ትልቅ ሚና ትጫወታለህ፡፡ እንደ አስተባባሪም ታገለግላለህ፡፡ በቪድዮ መልክ የቀረቡት ትምህርቶች በራሳቸዉ አስተማሪ ናቸዉ፡፡ መልመጃዎቹ እና ፈተናዎቹ ደሞ እንደ መገምገምያ ያገለግላሉ፡፡ የዉይይት መመሪያዎቹ ደሞ ተማሪዎች የተማሩትን በግልፅ መናገር እንዲችሉ ያግዛል፡፡ አሰልጣኝ ተማሪዎች በትክክለኛው መስመር ላይ መሆናቸዉን እና በኮርሶቹ ላይ የሚሰጡት ማቴሪያሎችን በሙሉ አቅም እንዲጠቀሙ ማገዝ አለበት በተለይም የኢንስቲቱቱን ባጅ/አርማ (የሚኒስትሪ እና የህይወት ክህሎት) በተመለከተ፡፡ ስለ አሰልጣኝ የስራ ድርሻ እና ስለ ኢንስቲቱቱ ፍልስፍና የበለጠ ለማወቅ "ተርድሚል ኢንስቲቱት የስልጠና መርህ" የሚለዉን ያንብቡ፡፡

### ምን አይነት ሰዎችን ይሰብስቡ?

በቡድንህ ዉስጥ እንዲካተቱ የምትፈልጋቸው ሰዎች አይነት እንደ ምርጫህ ነዉ፡፡ ለመማር የተሰጡ እና ጉጉት ያላቸዉ መሆናቸዉን ግን አረጋግጥ፡፡ ወደዚህ ፕሮግራም ለመግባት በቂ ጊዜ እና አቅም እንዳላቸው አረጋግጥ፡፡ ፕሮግራሙን ለመቀላቀል የወሰኑበት ምክንያት ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጥ፡፡ እሄንን ካረጋገጥክ የፈለከዉን ሰው ማስገባት ትችላለህ፡፡

ተርድሚል ኢንስቲቱት ስርአተ ትምህርት ሲሰራ ሪሶርስ የሚያጥራቸዉን ፓስተሮች፣ የቤተክርስትያ መሪዎች እናም ፓስተር እና መሪዎችን ሁሉ ታስቦ ነዉ፡፡ የኢንስቲቱቱ ባጅ/አርማ (ከስር ስለዚህ በደንብ ይገለፃል) ፓስተሮች/ መሪዎች በግል ህይወታቸዉም ይሆን በሚኒስትሪያቸዉ ለሚያጋጥማቸዉ ጥያቄዎች መልስ እንዲሆኑ ነዉ የተዘጋጁት፡፡ የባጅ/አርማ ጥቅም ለሁሉም ይሆናል ጥቅማቸዉን የበለጠ የሚያዩት ግን በቤተክርስትያን/ሚኒስትሪ ዉስጥ የሚያገለግሉ ናቸዉ፡፡

ተማሪዎች በሳምንት ከ3-5 ሰዓት በእራሳቸዉ የጥናት ጊዜ እንደሚኖራቸዉ እና አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ደሞ በቡድን ዉስጥ ከአሰልጣኝ ጋር ያሳልፋሉ ብለን እናስባለን፡፡ በእየሳምንቱ ለመገናኘት ካሰባቹኮርሱ ከ7-11 ሳምንት ይወስዳል፡፡ እያንዳንዱ ሰርተፊኬት ከ4-5 ኮርሶች ያካትታል፡፡ ወደ ቡድንህ ተማሪዎችን ከማስገባትህ በፊት በቅድሚያ ምን ያህል ሰዓት መስጠት እንደሚጠበቅባቸዉ፣ ምን ያህል ስራ እንደሚጠብቃቸዉ እና በየስንት ጊዜ መገናኘት እንዳለባቸዉ ማሳወቅ ይኖርብሀል፡፡

በመጨረሻም በአንድ ብድን ዉስጥ ስንት ሰዉ ሊኖር እንደሚገባ እናዉራ፡፡ አሰልጣኝ በመሆንህ ተማሪዎችህን ትከታተላለህ በየሳምንቱም ዉይይታቸዉን ትመራለህ፡፡ ለብዙ አሰልጣኞች ከ5-6 ሰው በላይ አንድ ቡድን ዉስጥ መያዝ አስቸጋሪ ነዉ፡፡ አንድ አንድ አሰልጣኞች ከ12-15 ሰዉ አንድ ቡድን ዉስጥ ሊኖራቸዉ ይችል ይሆናል፡፡ እኛ ግን እንደዚህ ትልቅ የሆኑ ብድኖችን ወደ ትናንሽ ቡድኖች ከፋፍለው የዉይይት መሪዎችን እንዲያስቀምጡ እንመክራለን፡፡ በቡድንህ እንድ ሰው ብቻ ቢሆንም ግን ችግር የለዉም፡፡

## ቡድኑ በየስንት ጊዜ ቢገናኝ ጥሩ ነዉ?

በየሳምንቱ ተገናኝታቹ ስለ ትምህርቱ ማቴሪያል እንድትወያዩ እንመክራለን፡፡ እሄ ትምህርቱን የበለጠ ለመረዳት እና ለመተግበር ያግዛል፡፡ በየሳምንቱ መገናኘት ግን ለሁሉም እንደማይቻል እናዉቃለን፡፡ ከላይ እንደገለፅነዉ ብድኑ በየስንት ጊዜ እንደሚገናኝ መብት ለአሰልጣኙ ተሰጥቶታል፡፡

3 ሰርተፊኬት = 1 ዲፕሎማ

ተርድሚል ኢንስቲቱት 3 የተለያዩ ሰርተፊኬቶችን ይሰጣል፡፡ ሶስቱም ከተጠናቀቁ ደሞ የኢንስቲቱቱን ዲፕሎማ በክርስትና ሚኒስትሪ ይሰጣል፡፡ የመጀመሪያው ሰርተፊኬት የመሰረት / ፋዉንዴሽን ሰርተፊኬት ይባላል፡፡ እሄ 4 ኮርስ የሚይዘው ሰርተፊኬት በመፅሀፍ ቅዱስ እና ስነመለኮት ጥሩ መሰረት ይጥላል፡፡ ቡድኖች ከዚህ መሰረት መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡ እሄንን ካጠናቀቁ በዉሀላ ቡድኖች ወደ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናቶች ሰርተፊኬት፣ ስነመለኮት ጥናቶች ሰርተፊኬት ወይም ወደ ሁለቱም ጥናት መቀጠል ይችላሉ፡፡ በኮርሶች መሀል ዕረፍት ከተወሰደ አንድ ሰርተፊኬት አንድ ዓመት አካባቢ እንዲወስድ ተደርጎ ነዉ የተሰራዉ፡፡ እንደ ቡድናቹ ዉሳኔ ግን ከዚህ ጊዜ ባነሰ ወይም በበዛ ጊዜ ሊጨረስ ይችላል፡፡

የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናቶች ሰርተፊኬት ተርድሚል የሚቀሩትን የብሉይ እና አዲስ ኪዳን ኮርሶችን ይይዛል፡፡ የስነመለኮት ጥናቶች ሰርተፊኬት ደሞ ከተርድሚል የሚቀሩትን የስነመለኮት ኮርሶችን ይይዛል፡፡ ሁለቱም ሰርተፊኬቶች አምስት ኮርሶችን ይይዛል፡፡ የፈለጋቹትን ሰርተፊኬት ማስቀደም ትችላላቹ፡፡ ሁለቱንም ሰርተፊኬቶች አንድ ላይ ከዚም ከዛም እያላቹ ማስኬድም ትችላላቹ፡፡

## የተርድሚል ኢንስቲቱት የኮርስ ዲዛይን/አወቃቀር

የተርድሚል ኢንስቲቱት ኮርሶች በዉስጣቸው የተርድሚል ተከታታይ ትምህርቶች እና ተጨማሪ ሰነዶችን እንደ የጥናት መመሪያዎች፣ የዉይይት መመሪያዎች እና የኢንስቲቱቱ ባጅ/አርማ (የሚኒስትሪ እና ህይወት ክህሎት) ይይዛል፡፡ ኮርሶቹ የኮርስ መመሪያዎች፣ ሳንታዊ ፈተናዎችን እና የመጨረሻ ፈተናም ይይዛል፡፡ የተርድሚል ኢንስቲቱት ስርአተ ትምህርት የ7-11 ሳምንት ኮርስ ለማድረግ በማሰብ 1-3 ተከታታይ ትምህርቶችን አቀላቅለናል፡፡ ለምሰሌ የስነመለኮት መሰረት ኮርስ የሐዋሪያው እምነት እና የስነመለኮት እድገት ድምር ነዉ፡፡ እሄም ስለሆነ የስነመለኮት መሰረት ሞጁል 7 በምስል ትምህርቶቹ እና ፅሁፎቹ ከስነመለኮት እድገት ትምህርት 1 ጋር አንድ መሆናቸዉን ታያላቹ፡፡ ተማሪዎችህ ግራ እንዳይጋቡ እሄንን አስቀድመህ ብታሳዉቃቸው መልካም ነዉ፡፡

## በኢንተርኔት ላይ የሚወሰደዉ የክፍል ጊዜ እና ሜሞሪ ካርድ

ተርድሚል ኢንስቲቱትን በደንብ መጠቀም የሚቻለዉ ኢንተርኔት ላይ ባለው የክፍል ጊዜ ነዉ፡፡ በinstitute.thirdmill.org ላይ በመግባት ተማሪዎች አካዉንት ይከፍታሉ፣ለኮርስ ይመዘገባሉ፣ ትምህርቶቹን ያያሉ፣ፈተና ይወስዳሉ እና የሚያስፈልጓቸዉን ሰነዶች ያወርዳሉ፡፡ እዚህ ላይ ተማሪዎችህን መከታታል ትችላለህ፡፡ ኢንተርኔት መጠቀም የማይችሉ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸዉን እንዲያገኙ ለማገዝ የሚያስፈልገዉን እዚው ገኛሉ፡፡ ሁሉም ማቴሪያል በሜሞሪ ካርድ እና ፕሪንት ለማድረግ ዝግጁ በሆነ መልክ ይገኛል፡፡ ኢንተርኔት የማያስፈልገዉን ሜሞሪ ካርድ ለማግኘት በ thirdmill.org/request ላይ የሚገኘዉዉ ፎርም ይሙሉ፡፡

ሁሉም ኮርስ በዉስጡ ከታች የተዘረዘሩት ይይዛል

- የኮርስ መመሪያ
- የኢንስቲቱቱ ባጅ/አርማ
- 7-10 ሞጁሎች
- የመጨረሻ ፈተና

## የኮርስ መመሪያ

የተርድሚል ኢንስቲቱት ኮርሶች ሁሉ የኮርስ መመሪያ ያካትታሉ፡፡ እሄ ሰነድ በኮርሱ ገፅ ላይ ከላይ የሚገኝ ሲሆን በሜሞሪ ካርዱም ላይ ይገኛል፡፡ የኮርሱንም ዓላማ እና አጠቃላይ መረጃ ይይዛል፡፡ በዉስጡ የኮርሱ መግለጫ፣ዓላማ፣ ኮርሱ ዉስጥ ያሉ ርዕሶች፣የአሳይመንት መመሪያዎች እና ለትምህርቱ ይዞት አስተዋፅኦ ያደረጉ ፕሮፌሰር እና ፓስተሮች ዝርዝር ይይዛል፡፡

## የኢንስቲቱቱ ባጅ/ አርማ (ሚኒስትሪ እና የህይወት ክህሎት)

ተርድሚል ኢንስቲቱትን ለየት የሚያደርገው አንዱ ነገር በየኮርሱ በሚኒስትሪ ባጅ/አርማ ላይ ቡድናቹ የሚሰራው ስራ ይሆናል፡፡ ለየኮርሱ የሚመደበው ባጅ/አርማ ይነገራል፡፡ ያንን ባጅ/አርማ ለማግኘት ሊደረጉ እና ሊሟሉ የሚገቡትን ተርድሚል ኢንስቲቱት ያሳዉቃል፡፡ ሁሉም የባጅ/አርማ ሰነድ በዉስጡ 4 ነገሮች ይይዛል፡፡ እነሱም ስለ ባጁ/አርማ የሚናገር የመግቢያ አንቀፅ፣ የባጁ/አርማ ይዘት፣ የዉይይት ርዕሶች እና የተግባር ጥሪ ናቸዉ፡፡ ኮርሱን ስትጀምሩ ወደ ተግባር ጥሪ ከመሄዳቹ በፊት ለዉይይት ርዕሶቹ በቂ ጊዜ እንድትሰጡ እናበረታታለን፡፡

የባጅ/አርማ ስራ ዉይይት እና የተግባር ጥሪን ጨምሮ ከ7-11 ሳምንት ወይም ከዛ በላይ በሚወስደው የኮርስ ጊዜ ላይ ሁሉም ሊካተት ይገባል፡፡ አሰልጣኝ እንደመሆንህ ስለባጅ/አርማ የተረዳህዉን በመጠቀም የባጅ ስራዉን ታስተባብራለህ በመጨረሻም ተማሪው የሚጠበቅበትን ካሟላ ባጁ ሊሰጠው እንደሚገባ ማመንህን ታረጋግጣለህ፡፡ ባጁ በዉስጡ ስለ ማስተማር፣መሪነት፣የቤተክርስትያን ህይወት፣ፀሎት፣ ወንጌል ስርጭት እና የመሳሳሉት አይነት ርዕሶች ይይዛል፡፡

ሁሉም ሞጁል በዉስጡ የሚከተሉትን ይይዛል

1. የምስል ትምህርቶች/ፅሁፎች/ድምፆች
2. የጥናት መመሪያዎች
3. የሙከራ ፈተና
4. የዉይይት መመሪያዎች/በማህበረሰቡ ዉስጥ የመማሪያ ጊዜ
5. የመጨረሻ/ማጠቃለያ ፈተና

## 1. የምስል ትምህርቶች/ፅሁፎች/ድምፆች

የየትኛዉም ስርቸት ትምህርት ቁልፍ ይዘቱ እና ይዘቱ የሚሰጥበት መንገድ ነዉ፡፡ ተርድሚል ኢንስቲቱት በተርድሚል ሚኒስትሪ በኩል በሚያገኛቸው ጥራት ያለው የምስል፣ፅሁፍ እና ድምፅ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ስርአት ትምህርት ተባርኳል፡፡ ተማሪዎች በአወቃቀራቸው ጥራት ምክንያት ሽልማት ያገኙ ምስሎችን፣በተለያዩ የዓለማችን ክፍል ካሉ ፓስተሮች እና ፕሮፌሰሮች ጋርየተደረጉ ቃለ መጠይቆችን እና ወጥ የሆኑ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ያያሉ፣ያነባሉ ወይም ያዳምጣሉ፡፡

## 2. የጥናት መመሪያዎች

ተርድሚል ኢንስቲቱት ትምህርቶች ለመረዳት ቀላል እና ግልፅ በሆነ መልክ ቢፃፉም አንድ አንድ ርዕሶች ከበድ ሊሉ ይችላሉ፡፡ እንዳንዱ ትምህርት አንድ ፕሮፌሰር በብዙ የክፍል ጊዜዎች ሊያስተምር ከሚችለው በላመረጃ ሊይዝ ይችላል፡፡ ተማሪዎች የሚማሩትን በጥልቀት ማየት እንዲቻል ለሁሉም ሞጁል የጥናት መመሪያዎች አዘጋጅተናል፡፡ የጥናት መመሪያዎቹ በዉስጣቸው የተለያዩ ምድቦች እና የሰዓት ኮዶችን ወደ የተለያዩ ክፍሎች ይከፋፍላል፡፡ ክፍሎቹ ሁለት ነገር ይይዛሉ እነሱም ማስታወሻ ለመያዝ የሚረዱ ሀሳቦችን እና ለሞጁሉ ፈተና የሚያግዙ መልመጃዎች ናቸዉ፡፡ እንደ አሰልጣኝ ተማሪዎች እነዚን የጥናት መመሪያዎችን በየሳምንቱ እየተጠቀሙ መሄዳቸዉን ማረጋገጥ አለብህ፡፡

## 3. የሙከራ ፈተና

ሁሉም ሞጁል በየጊዜው የሚሰጡ ፈተናዎች አሉት፡፡ ፈተናዎቹም ምርጫ፣ እዉነት/ሀሰት እና አዛምድ ጥያቄዎችን ይይዛሉ፡፡ ተማሪው የትምህርት ምስሉን ካየ፣ማስታወሻ ከወሰደ እና በደንብ ካጠና በዉሀላ የሙከራ ፈተና መዉሰድ ይጠበቅበታል፡፡ ፈተናው የ20 ደቂቃ (1 ደቂቃ ለአንድ ጥያቅ) ነዉ፡፡ ፈተናዉን ለማለፍ እና ኮርሱን ለማጠናቀቅ ተማሪው በትንሹ 80% ዉጤት ማምጣት አለበት፡፡ ተማሪው ከ80% ነጥብ ዉጤት በታች ካመጣ ፈተናዉን ደግሞ መዉሰድ ይችላል፡፡ ፈታናው እንደገና እንዲከፍትለት ግን 1 ሰዓት ያህል መጠበቅ አለበት፡፡ በዛ አንድ ሰዓት ተማሪዎች በደንብ አጥብተው ዳግም ፈተናዉን ለመዉሰድ እንዲዘጋጁ እንመክራለን፡፡ ተማሪዎች የማለፍያ ዉጤት እስኪያመጡ ድረስ የፈለጉት ጊዜ ፈተናዉን ደጋግመው መዉሰድ ይችላሉ፡፡

እንደ አሰልጣኙ ምርጫ ቢሆንም ግን አሰልጣኙ ተማሪዎች ወደ ሳምንታዊ የዉይይት ስብሰባ ከመምጣታቸው በፊት አጥንተው የሙከራ ፈተናዉን አልፈው እንዲመጡ አንዲያደርግ እናበረታታለን፡፡ እሄን በማድረግ ተማሪዎች የኮርሱን ማቴሪያል እንደተረዱ እና በቡድን ዉስጥ ለመወያየት ዝግጁ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፡፡

## 4. የዉይይት መመሪያዎች/በማህበረሰቡ ዉስጥ የመማሪያ ጊዜ

እስከ አሁን ካየናቸዉ ነገሮች ተነስተን ተማሪዎችን ከመከታተል በቀር አሰልጣኝ ሌላ ስራ የለዉም እያላቹ ይሆናል፡፡ ትምህርቱ በምስል እና ፈተና መልክ ይሰጣል፡፡ ተርድሚል ኢንስቲቱት ግን በዉይይት ቡድኖች መሀል ስላለዉ የፊት ለፊት መስተጋብር ትልቅ ቦታ አለው፡፡ አንተ አሰልጣኑ ደሞ እዚህ ላይ ትልቅ ሚና ትጫወታለህ፡፡ ተማሪዎች በየሳምንቱ ከሞጁሉ ስለተማሩት ለማወያየት የምትጠቀምባቸው የዉይይት መመሪያዎች አሉ፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ የዉይይት ጊዜዎች የተማሩትን አካል የሚያለብሱበት እና ወደ ሚኒስትሪያቸው እና ወደ ከእግዝአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ጋር የሚያመጡበት መንገድ ነዉ፡፡

የዉይይት መመሪያዎቹ ሁለት ነገር ይይዛሉ፡፡ በመጀመሪያ ገፅ የዉይይት ጥያቄዎች በሁለተኛው ገፅ ደግሞ የአንድ ነገር ጥናት፣ የክለሳ ሀሳቦች እና ጥያቄዎችን ይይዛሉ፡፡ አሰልጣኙ ከዉይይት መመሪያው ዉስጥ የፈለገዉን መጠቀም ይችላል፡፡ የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ አሰልጣኙ ጠንካራ እና ጤናማ የዉይይት ጊዜ መምራት እንዲችል ማገዝ ነዉ፡፡፡ ዉይይቶቹ ከ1-1፡30 ሊወስዱ ይችላሉ እንደ ቡድኑ ትልቀት እና አስፈላጊነት ግን ሰዓቱ ሊበዛም ሊያንስም ይችላል፡፡ አሰልጣኙ የዉይይት መመሪያዉን ለመጠቀም ካሰበ ግን አስቀድሞ ለተማሪዎቹ የዉይይት ጥያቄዎቹን መመለስ እና መወያየት እንደሚጠበቅባቸው ማሳወቅ አለበት፡፡

በዉይይቱ ጊዜ የአሰልጣኙ ሌላኛዉ የስራ ድርሻ ሁሉም ሰዉ በበቂ ሁኔት ዉይይቱ ላይ እየተሳተፈ መሆኑን ማረጋገጥ ነዉ፡፡ አንድ አንድ ሰዎች ብዙ ያወራሉ ሌሎች ደሞ ትንሽ ያወራሉ፡፡ አንድ ሰዉ ብቻ ዉይይቱን የሚቆጣጠር እና ሌሎችን የማያስወራ ከሆነ የምታርምበትን ጥሩ መንገድ መፈለግ አለብህ፡፡ ማዉራት የማይፈልጉ ሰዎችም ካሉ ማበረታታት እና የነፃነት ስሜት እንዲሰማቸዉ ማገዝ አለብህ፡፡

## 5. <u>የመጨረሻ/ማጠቃለያ ፈተና</u>

አንድ ኮርስ ሲያልቅ 60 ጥያቄ የሚይዝ የመጨረሻ ፈተና አለው፡፡ እንደ ሙከራ ፈተናው ተማሪዎች በትንሹ ለማለፍ 80% ማምጣት አለባቸው፡፡ ካላለፉም ደጋግመው መዉሰድ ይችላሉ ፡፡ ብቻ በሙከራቸዉ ጊዜ መሀል 1ሰዓት እየጠበቁ፡፡